## የሐላል ኢንዱስትሪ

የሐላል ኢንዱስትሪ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እድገት እያሳየ ያለ አዲስ የንግድ አቅጣጫ ሲሆን። በተለይ ከ ‘’Covid-19’’ በኃላ በርካቶች ለሐላል ምርቶች እና አገልግሎቶች ያላቸው ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል። በግሎባል ኢስላሚክ ኢኮኖሚ ሪፖርት መሠረት የሐላል ፍላጎት ያላቸው ተጠቃሚዎች ለሐላል ምርቶችና ግልጋሎቶች ወጪ ያደረጉት 4 ትሪሊዮን ዶላር እንደሚደርስ ይገመታል።ይህም በአንድ አመት ውስጥ የተደረገ ወጪ ነው።

የሐላል መድሃኒት ምርቶች፣ የሃላል ኮስመቲክስ፣ የሐላል ምግብና መስተንግዶ፣ የሐላል ትራቭል የመሳሰሉት በመጪው ጊዜ የዓለማችንን የንግድ ሂደት አቅጣጫ በማስያዝ ረገድ ያላቸው ተጽዕኖ በጣም ከፍተኛ ነው።

## የሐላል ኤክስፖና ሰሚት

የሐላል ምግብና ቱሪዝም ኤክስፖ ‘’ከኢድ እስከ ኢድ ጉዞ ወደ ሃገር ቤት’’ በተሰኘው መርኃ ግብር ውስጥ የሚከናወን ሲሆን፤ በርካታ ቀጥር ባላቸው የሃገር ውስጥና የውጪ ሃገር ሰዎች ይጎበኛል። በዚህ ኤክስፖ ላይ የምግብና መጠጥ አምራቾች፣ የግብርና ምርት አቅራቢዎች፣ የሆቴልና መስተንግዶ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣የሐላል አስጎብኚ ድርጅቶች በስፋት ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃሉ። በዚህ ኤክስፖና ሰሚት ላይ በሐላል ኢንዱስትሪ ውስጥ ባለድርሻ የሆኑ አካላት የሚገናኙበት፣ አብረው የሚያቅዱበት፣አብረው የሚሰሩበትና መጪውን ጊዜ አብረው በመሆን እጅግ ግዙፍ ከሆነው ኢንዱስትሪ በስፋት የሚጠቀሙበትን እድል ያገኛሉ።

ከኤክስፖው ጎን ለጎን በሚካሄደው ሰሚት ላይ  የተለያዩ ይዘት ያላቸው ርዕሶች ይዳሰሳሉ። የሐላል ሰርተፊኬሽን እና በኤክስፖርቱ ላይ ያለው ሚና፣የሐላል ሰርተፊኬሽን ለሐላል ፋይናንስ ተቋማት ስኬት የሚኖረዉ ሚና፣ የሐላል ኢንዱስትሪና የአፍሪካ ቀንድ የኢኮኖሚ ትስስር፣ የሐላል ኢንዱስትሪ ያቀፋቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶች እና የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

## የኤክስፖው ተሳታፊዎች (Exhibitors)

- የምግብና መጠጥ አምራቾች
- የግብርና ምርት አቅራቢዎች
- የችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች (ሱፐርማርኬት፤ ሐይፐር ማርኬት)
- የምግብ ግልጋሎት ሰጪዎች
- ሆቴልና መስተንግዶ
- የሐላል ፋይናንስ ተቋማት
- የሐላል አስጎብኚና ጉዞ ላይ የተሰማሩ
- የመንግስት ተቋማት

## የፕሮግራሙ ይዘቶች

- በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ጽሁፎች ይቀርባሉ
- የተለያዩ ምርቶችና ግልጋሎቶች ኤግዚቢት ይደረጋሉ
- የንግድ ለንግድ ትስስሮች በጥልቀት ይካሄዳሉ
- የሐላል ምግብ አቅራቢዎች ተሞክሯቸውን ያካፍላሉ
- የመክፈቻና የመዝጊያ ፕሮግራሞች

## ጎብኚዎች

- የምግብ አስመጪና ላኪዎች
- ኢንቨስተሮች
- ኢንተርፕሮነሮች
- የኤምባሲ ተወካዮች
- የሚድያ ባለሙያዎች
- የማህበራዊ ሚድያ ተጽዕኖ ፈጣሪዎች
- የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና መምህራን
- ባጠቃላይ ሰፊው ማህበረሰብ ይገኛሉ።

## የፕሮግራሙ ዓላማዎች

1. ኢትዮጵያውያን ላኪዎች በተቀባይ ሃገራት ግዴታ እየሆነ ስለመጣው የሐላል ሰርተፊኬሽን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ዝግጅት እንዲያደርጉ ማገዝ
2. ኢትዮጵያ ከሐላል ቱሪዝም መጠቀም የምትችልበትን እድል መፍጠር
3. በሐላል ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ ዋና ዋና አካላትን ማገናኘትና ፈሪያማ ትስስር እንዲፈጥሩ ማስቻል
4. ስለ ሐላል ኢንዱስትሪ ግዝፈትና ይዘት የግንዛቤ ማስጨበጥ
5. ተግባራዊ የሆኑ የንግድ የመፍትሄ አቅጣጫዎች መጠቆምና በሐላል ኢንዱስትሪ ውስጥ ያሉ አዳዲስ የንግድ ሐሳቦችን ማሳየት
6. በሐላል ኢንዱስትሪ የተሰማሩ አቅራቢዎችን ከተጠቃሚዎቹ ጋር ማገናኘት